# ልብ እኩል ከሆነ

ከእንግዳ ታደሰ

ያኔ ጨቅላ ሳለሁ ስድስተኛ ክፍል፣
ስለልብ ስማር ስነፍጥረት አካል፣
ሁሉም ሰው ልብ አለው ጭብጦ የምታህል፣
ለሁሉም የአዳም ልጅ ጥቁር ነጭ ሳትል፣
ደም ቅዳ፣ ደም መልስ፣ ግራ ቀኝ ኦሪክል፣
የደም ዝውውሩን የእስትንፋሱን እስኬል፣
አጣምራ የያዘች ሁሉንም በጥቅል።
እያሉ ያስተማሩኝ የሳይንስ መምህሬ
ያለፃፉኝ አለ ከሳይንስ ደብተሬ
ሁሉም ልብ ካለው አንድ አይነት በሙሉ
ለምን ይለያያል ወኔውና ውሉ
እኔም ልብ አለችኝ...
ደም ቅዳ ደም መልስ ሁሉንም የያዘች
ያቀን ሲመጣ ግን ድፍረቱን ታጣለች
ምን አገባህና እንዳትገባ ደፍረህ ብላ ትለኛለች
መቂናጥዋ ጠዞ ፍፁም እየራደች
ታዲያ የሁሉም ሰው ልብ አንድ ከሆነ
የኔ ከታዬ ጋር በምን ተለያየ?

ለዶክተር ታዬ ወ/ሰማያት መታሰቢያ